# ሞጁል 1

## የአሰልጣኙ መምሪያ

## የማብዛት ተልዕኮ ስልጠና

### ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል

multiplication network

*more churches, stronger churches*

ማታወሻ፡- በአሰልጣኙ መምሪያ ላይ የተሰመረባቸው ቃላት እና ሐረጎች በተሳታፊው መምሪያ ላይ ቃላቶቹ ወይንም ሐረጎቹ ሳይገቡ ክት ስፍራ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በዚህ ማሰልጠኛ ሞጁል ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ለተሳታፊዎች ማኑዋል እደ መልስ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ትርጉም፤ ሚልክያስ ለዕላጎ ሸምሱ - 2012

# የማብዛት ተልዕኮ
# የጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ ሞጁል
# መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስተሪስ
# ብዙ አጥቢያ ያላት/ ጠንካራ ቤተክርስቲያን

2007 ዓ.ም

ይህ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ማኑዋል በAbridged Omega Course እና Multiplication Network Ministries’ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የተሰኘ የማስተማሪያ መጽሐፍትን በማዋሃድ የተዘጋጀ ነው፡፡

MNM ከ Training Center for Church Planters እና ከ World Ministries ባገኘው ፈቃድ መሰረት ይህን ማስተማሪያ ለቤተክርስቲያን ጥቅም እንዲህ አቅርቦታል፡፡

እናንተም ይህን ማስተማሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጠበቂያዎች እስከተከተላችሁ ድረስ ይህን መጽሐፍ እንድታባዙና እንድታሰራጩ እንደ ማበረታቻ የሰጠናችሁ ፈቃድ ይሁንልን፡፡

1. ለመጽሐፉ ጸሐፊያን እና ተርጓሚያን ዕውቅና መስጠት
2. መጽሐፉ ላይ ማሻሻያ አድርጋችሁ እንደሆን እርሱን ማሳወቅ
3. ለማሳተሚያ ካወጣችሁት ዋጋ በላይ አለማስከፈል እና
4. ከ አንድ ሺህ ኮፒ በላይ አለማሳተም

ኦሜጋ ኮርስ፡-

ተግባራዊ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ማስተማሪያ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክፍለትምህርት 6 | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ I: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲናገረን መፍቀድ | የጸሎት ኮንሰርት: መዝ 95 | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዴ: ስልትን መተርጎም | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ 3: የእግዚአብሔርን ቃል መተርጎም | መሪ ዕቅድን ማቅረብ | የጸሎት ኮንሰርት እግዚአብሔርን ስለታማኝነቱ ማመስገን |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | አምልኮ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | የጽንሰ አሳብ ውህደት | አምልኮ |
| | **ሞጁል 7**<br>**ቡድን መገንባት** | **ሞጁል 8**<br>**ቡድን መገንባት** | **ሞጁል 9**<br>**ሰዎችን መንከባከብ** | **ሞጁል 10**<br>**ቤተክርስቲያንን መመስረት** | **ሞጁል 11**<br>**ለወደፊት ማቀድ** | **ሞጁል 12**<br>**በአንድነት ወደፊት መንቀሳቀስ** |
| ማጥኛዎች | በወንጌል የተለወጠ | ለትሁታን ጸጋን ይሰጣል | ፍቅር፤ የአገልግሎት መሰረት | ዓለምን ያምን ዘንድ: ዮሐ 17 | ዋጋን መተመን | ዓለም ሁሉ እስኪሰማ! |
| ክፍለትምህርት 1 | የቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የቡድን ስራ: ከሌሎች ጋር ውጤታማ በሆነ መልኩ መስራት | በአብሮነት ውስጥ የሚደረግ የወንጌል ስርጭት | የቤተክርስቲያን ጥምር ተግባራት | የባለአደራነት ትምህርትን መተዋወቅ | ግጭትን መፍታት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | መሪዎችን ማስታጠቅ | ወንጌል | የጽንሰ አሳብ ውህደት | የግብአት ባለአደራ | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 2 | ቤተክርስቲያን: A Living Organism | ቡድን ማደርጀት | የቡድን አባላትን መንከባከብ | በጸጋ ስጦታዎች ማገልገል | የገንዘብ ባለአደራ | ንስሃ እንደ የሕይወት ዘይቤ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ቡድን ማደርጀት | ህብረት | የጸጋ ስጦታው ተለይቶ የሚሰማራ የክርስቶስ አካል | የንብረት ባለአደራ | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 3 | መቼ ነው አንድ ቡድን ቤተክርስቲያን የሚባለው? | የቡድን ውይይት ሂደት | ማህበረሰባችንን መንከባከብ | የጸጋ ስጦተ መለያ ቅጹን መጠቀም እንዴት ይቻላል | የስልታዊ ዕቅድ ሰርቶ ማሳያ | ተቃውሞ እና ተሃድሶ: የቤተክርስቲያን ስርአት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ደቀመዝሙር | ወንጌል፣ አውድ እና አውዳዊነት | የጸጋ ስጦታው ተለይቶ የሚሰማራ የክርስቶስ አካል | | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 4 | ከመጽሀፉ አሳብመውሰድ 4: ከመጽሐፉ አሳብ የመውድ ጥናት መንገዶች | አዳዲስ የቡድን መሪዎችን ማሰልጠን | የሚያድግ ቤተክርስቲያን መገለጫዎች | የመንፈሳዊ ውጊያ ሂደት | | ሌሎችን ለአገልግሎት ማሰማራት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ደቀመዝሙር | ደቀመዝሙር ማድረግ እና መሪዎችን ማስታጠቅ | የጽንሰ አሳብ ውህደት | ህብረት | | መሪዎችን ማስታጠቅ |
| ክፍለትምህርት 5 | የክርስቲያን መሪ ፕሮፋይል | የተግባቦት ዘይቤ | አገልጋይ መሪነት | ቤተክርስቲያንን ወደ አምልኮ መምራት | | ትልቁ የክርስቶስ አካ፤ ቤተክርስቲያናችን እና ማህበረሰብ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | መሪዎችን ማስታጠቅ | መሪዎችን ማስታጠቅ | መሪዎችን ማስታጠቅ | አምልኮ | | ህብረት |
| ክፍለትምህርት 6 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 1: መልዕክቱን መረዳት | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 2: አድማጭን መረዳት | የጸሎት ኮንሰርት: ኤፌ 3-5 | መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት 3: ሰባኪው እንደ ግለሰብ | | የጸሎት ኮንሰርት: ወንጌልን ለማሰራጨት መጸለይ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | አምልኮ | አምልኮ | ህብረት | ህብረት | የግብአት ባለአደራ፤ ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል |
| | | | | | | |

| | ለአንድ ቀን ለስጠና የጊዜ ደዘት እንደ ምሳሌ የቀረበ | |
|---|---|---|
| | የሞጁል አንድ መግቢያ 1 | 2:00 |
| | የትምህርቱ ትኩረት መግለጫ፡- የጤናማ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | 2:15 |
| | ሪፖርት ማቅረብ | 2:30 |
| ክፍለ ትምህርት አንድ | ጤናማ ቤተክርስቲያን ምንድን ነው | 3:00 |
| | ረፍት | 4:00 |
| ክፍለ ትምህርት ሁለት | ጤናማ ቤተክርስቲያን የሚተክል አገልጋይ ምንድን ነው | 4:15 |
| ክፍለ ትምህርት ሶስት | "የመጨረሻ" አሳቤ፡- እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል | 5:15 |
| | የምሳ ረፍት | 6:15 |
| ክፍለ ትምህርት አራት | የቤተክርስቲያን ተከላ ዙር ሂደት | 7:15 |
| ክፍለ ትምህርት አምስት | ትናንሽ ቡድኖች ለምን አስፈለገ | 8:15 |
| | የሻይ ረፍት | 3:15 |
| ክፍለ ትምህርት ስድስት | ከመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ወደሕይወት የሚቀዳ ጥናት1፡- መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስተምረን መፍቀድ | 9:30 |
| | መዝጊያ | 10:30 |
| | የቀኑ ጥናት ፍጻሜ | 10:45 |

# ጤናማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት

## ሞጁል 1

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተሳታፊዎቹ በራሳቸው አገላለጽ የሚከተሉን ሐሳቦች ይናገራሉ

- ➢ ጤናማ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነ
- ➢ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እና
- ➢ ጤናማ ቤተክርስቲያንን ለመትከል የሚጠቅሙ መሰረታዊ ሂደቶች

### የሞጁል አንድ መግቢያ

አሰልጣኙ እንደመግቢያ የሚጠቀምበት ጥቆማ (2 ደቂቃ)

- ተሳታፊዎቹን ሞቅ ባለ፣ ወዳጅነትን በሚያሳይ እና ከልብ በሆነ ፍላጎት የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ማድረግ
- አጠር ያለ የመክፈቻ ጸሎት በማድረግ ቀኑን ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት

### ለትውውቅ ጊዜ መውሰድ (5 ደቂቃ)፡- ሶስት ቃላት

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- ተሳታፊዎቹ ማንነታቸውን ይገልጻል ብለው የሚያምኑትን ሶስት ቃላት እንዲያስቡ እድል መስጠት
- ለተሳታፊዎች ምን ያህል ሰው በቡድኑ እንዳለ ማሳወቅ እና እያንዳንዱ ሰው እየዞረ ሁሉንም ተሳታፊዎች እንዲተዋወቅ እና ማንነቴን ይገልጣል ብሎ ያሰበውን ሶስት ቃላት ለሚተዋወቃቸው ሰዎች እንዲናገር አራት ደቂቃ መስጠት
- በመጨረሻም ከተሳታፊዎቹ ውስጥ በተሰጠው አራት ደቂቃ ውስጥ ሁሉንም ሰዎች መተዋወቅ የቻሉ እንዳሉ አረጋግጥ፡፡ ይህን ለማወቅ እያንዳንዳቸው ምን ያህል ሰዎችን በተሰጣቸው ደቂቃ መተዋወቅ እንደቻሉ መጠየቅ በቂ ነው፡፡ ለምሳሌ የተሳታፊዎቹ ቁጥር 20 ቢሆን ምን ያህል ሰው አስርና ከዚያ በላይ ሰው እንደተዋወቀ፤ ምን ያህሉ 15 ሰዎች ተዋወቁ እና ምን ያህሉ 20 ሰዎች ተዋወቁ? በተቻለ መጠን ጊዜው የሚታወስ የደስታ ጊዜ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ፡-

እንዴት ናችሁ ስሜ ሚሮን ይባላል፤

ራሴን እንዲህ በሶስት ቃል እገልጠዋለሁ፤ ነገሮችን የማወቅ ጉጉት ያላት፣ ታጋሽ እና ትጉህ ሰራተኛ

**ጤናማ የሆኑ እና ጤናማ ያልሆኑ ቤተክርስቲያናት እንቅስቃሴ (8 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** የዚህ ተግባራዊ ልምምድ አላማ፤ ተሳታፊዎች ቀዳሚ ትኩረታቸውን ለቤተክርስቲያን ተከላ አስፈላጊ በሆኑ ግብአቶች ማስተም ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ላይ እንዲያደርጉ ነው፡፡

- **እንዲህ በል፡-** "እያንዳንዳቹ እጅግ ጥልቅ የሆነ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ልምዳችሁን ወደዚህ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና እንዳመጣችሁ አምናለሁ፡፡ የዚህ ስልጠና ዋናው አላማ የጤናማ ቤተክርስቲያን ባህሪያትን ለመዘርዘር እና ጤናማ ቤተክርስቲያ ለመገንባት ምን አይነት ዋጋ ይጠይቃል የሚለውን ለመገንዘብ ነው፡፡"
- ብዙ ቁጥር ያላቸውን ቡድኖች ለሁለት መክፈል፤ ከዚያም የመጀመሪያው ቡድን የጤናማ ቤተክርስቲያን መገለጫዎች ምን እንደሆኑ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ያላቸውን ልምድ ተጠቅመው የሚችሉትን ያህል እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት በተመሳሳይ ሌላኛውም ቡድን እንዲሁ እንዲያደርግ እድል መስጠት፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን የጻፈውን ዝርዝር የሚያቀርብበት አንድ ደቂቃ ስጥ
- **እንዲህ በል፡-** "ዛሬ የብዜት መረብ አገልግሎት የጤናማ ቤተክርስቲያን ባህሪያት ናቸው ብሎ ያወጣቸውን አስር መስፈርቶች እንመለከታል፡፡ በቅድሚያ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የሚያስፈልግበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶችን እየተወያየን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡"

# የጤናማ ቤተክርስቲያናት

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች (15 ደቂቃ)

የመክፈቻ ተግባር (2 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ተሳታፊዎች አዳዲስ ቤተክርስቲያን መትከል የሚያስፈልግበትን ምክንያት እንዲያስረዱ እድል ስጥ፡፡ ከዚያም በዚህ ክፍለ ትምህርት ተሳታፊዎች የጠቀሱት ምክንያት መጠቀስ አለመጠቀሱን በጥሞና እንዲያደምጡ ማበረታታት፡፡

ለእያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመክንዮ የሚነበበውን ክፍል ተሳታፊዎች ተከፋፍለው፤ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለቡድናቸው ያንብቡ፡፡ ከሚነበበው ክፍል ውስጥ ደግሞ በተሳታፊዎች መምሪያ ላይ ባለው የዚህ ትምህርት ክፍል ክፍት በታ ላይ የሚሞላውን ቃል እንዲፈልጉ እና እንዲሞሉ ምሩቸው፡፡

**የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (13 ደቂቃ)**

ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የሚያስፈልግበትን እውነት የሚያስረዱ አምስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመክንዮዎች አሉ፡-

1. **ምክንያቱም እግዚአብሔር <u>አብ</u> የጠፉትን <u>የሚፈልግ</u> እና <u>የሚያገኝ</u> ስለሆነ፡፡**

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዘፍ 3፡9፤ መዝ 23፤ ሉቃ 14፡15-24

2. **ምክንያቱም <u>የክርስቶስ</u> <u>ፍቅር</u> ግድ ስለሚለን፡፡**

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 2ቆሮ 5፡14-20፤ ማቴ 18፡12-14፤ ዮሐ 14፡23

3. **ምክንያቱም <u>መንፈስ ቅዱስ</u> ለሰው ዘር በሙሉ ስለተሳከ፡፡**

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሐዋ 2፡5-11፤ 10፡44-48፤ 1፡8

4. **ምክንያቱም አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የእግዚአብሔር መንግስት <u>ክፍል</u> ስለሆኑ፡፡**

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 1ጴጥ 2፡5፣ 9-10፣12 ፤ ቆላ1፡13-23፤ ሮሜ 12፡4-8

5. **ምክንያቱም አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን መትከል ለ<u>እግዚአብሔር</u> <u>ክብርን</u> ስለሚያመጣ፡፡**

### የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሉቃ 1:1-14፤ ራዕ 7:9-12

## ሪፖርት ማቅረብ

**የአሰልጣኙ መምሪያ ቅኝት:-** በዚህኛው ሞጁል ምንም አይነት ሪፖርት ተሚያስፈልገው ነገር ስለሌለ ይህን ጊዜ ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ተጠቀም:- 1) የጠቅላላውን ትምህርት ቅኝት ዳሰስ እና 2) ከዚያም ለሁሉም ትምህርቶች/ሞጁሎች ሪፖርት እንደሚያስፈልግ በማስረዳት ሪፖርት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስረግጠህ ተናገር።

የመብዛት ተልዕኮን መሰረት ያደረገ ጤናማ ቤተክርስቲያናትን የመትከል ቅኝት (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-**

- ተሳታፊዎች በመመሪያ መጽሐፋቸው ላይ ባለው ስዕላዊ መግለጫ ላይ አምስቱን ደረጃዎች ከመጀመሪያው ወይንም ከወንጌል ስርጭት ጀምረው እስከመጨረሻው ማስትም አምልኮና እገልግሎት ድረስ ያስፍሩ።

## ቤተክርስቲያን የመትከል አምስቱ ደረጃዎች




## ጤናማ ቤተክርስቲያናትን የመትከል ቅኝት ሪፖርት (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-**

- ተሳታፊዎች በተሰጣቸው መጽሐፍ ላይ ያለውን የትምህርቱን ቅኝትን በአትኩሮት እንዲያጤኑ አበረታታቸው::
- የትምህርቱን አደረጃጀት አብራራላቸው (እያንዳንዳቸው 6 ክፍለትምህርት ያላቸው 12 ሞጁሎች)
- ተሳታፊዎች ስድስቱንም ክፍለትምህርቶች እንዲያነቡ እና እያንዳንዱ ክፍለትምህርት ከአምስቱ ቤተክርስቲያን ከሚያስፈልጉ ደረጃዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኙ እንዲገልጹ አበረታቱአቸው::
- 12ቱን ሞጁሎች ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ጊዜ እና ሌሎች ግብአቶች ምን ሊሆን እንደሚችል አብራራ::
- ከዚያም ተሳታፊዎች የስልጠናውን አደረጃጀት፣ ስለሚያስፈልገው ጊዜ እና ሌሎች ግብአቶች የሚያነሱትን ጥያቄዎች ለመቀበል እና መልስ ለመስጠት ጊዜ ስጥ::

- ተሳታፊዎች በመጽሐፋቸው ላይ የተቀመጠውን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ሀ.ሰ.መ ወርሃዊ ሪፖርት የሚለውን ክፍል እንዲመለከቱ በማድረግ ሪፖርቱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አብራርተህ አስረዳ፡፡
- እንዴት አድርገው የሪፖርቲንግ ቀጹ ላይ መሙላት እንደሚቻል አስረዳ
- ተሳታፊዎች እንዴት አድርገው ከሞጁል 2 እስከ 12 ድረስ ያለውን ትምህርት አንዳቸው ለሌላቸው ሪፖርት እንደሚያደርጉ አስረዳ፡፡

# የቤተክርስቲያን ተከላ ሪፖርት

ወርሃዊ ሪፖርት

## ጠቅላላ መረጃ

| ሪፖርቱ የተደረገበት ወር | | የምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ተከናውኗል | አዎን | የለም |
|---|---|---|---|---|

| | |
|---|---|
| የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ስም | |
| ቤተክርስቲያኒቱን የሚተክለው ሰው አካባቢ | |
| የአካባቢው አስተባባሪ | |

| **ግስሰቦች** | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| **በቅርቡ የተዋወካቸው ሰዎች**<br>ቤተክርስቲያን ለመትከል ታስቦ ወንጌልን ለማድረስ የተዋወካቸው ሰዎች | | |
| **ወደጌታ የመጡ አዳዲስ ሰዎች**<br>የኢየሱስ ተከታዮች | | |
| **በቅርብ የተጠመቁ ሰዎች**<br>በጥምቀት ስርአት የተሳተፉ ሰዎች | | |
| **በስልጠና ላይ ያሉ አዳዲስ መሪዎች**<br>ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚመለመል ሰው ለመሪነት የሰለጠነ ነው | | |

**አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት ቡድን| በትንሹ ሁለት ደቀመዝሙር እና አንድ መሪ**

| | ወርሃዊ ግብ | ወርሃዊ ውጤት |
|---|---|---|
| **አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች**<br>በዚህ ወር የተጀመሩ ቡድኖች | | |
| **በትናንሽ ቡድኖች የተካተቱ አዳዲስ ተሳታፊዎች**<br>በዚህ ወር በትናንሽ ቡድኖች መሳተፍ የጀመሩ አዳዲስ ሰዎች | | |
| **የቡድን መሪ የሆኑ አዳዲስ መሪዎች**<br>በቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ክትትል የሚደረግለት ቡድን መሪ የሆነ አዲስ መሪ | | |

## የጸሎት ርዕስ

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________

## ምስክርነት

ከዚህ በታች ያለው ክፍት ቦታ የመጨረሻ ሳይሆን እንደመነሻ የቀረበ ሲሆን ተጨማሪ ወረቀት መጠቀም ይቻላል

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

# ክፍለ ትምህርት 1

# ጤናማ ቤተክርስቲያን

## ምንድን ነው? (60 ደቂቃ)

**ለመማር የሚጠቅም ታሪክ፡- ጤናማ ያልሆነ አንድ ቤተክርስቲያን ታሪክ** (10 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ይህ ለመማር የሚጠቅም ታሪክ ተሳታፊዎች የተፈጠረ እውነተኛ የሕይወት ውጣውረድን ወደማወቅ እና ለስረ የጤናማ ቤተክርስቲያን ባህሪያትን ወደመረዳት ይመራል፡፡ ይህ ለመማር የሚጠቅም ታሪክ የሚጀምረው ጤናማ ባልሆነ መልኩ የተተከለ ጤናማ ያልሆነ ቤተክርስቲያን ምን እንደሚመስል በመዘርዘር ነው፡፡

- ተሳታፊዎች "ጤናማ ያልሆነ ቤተክርስቲያን ታሪክ"ን ያንብቡ
- ተሳታፊዎች ቤተክርስቲያኒቱን ጤናማ እንዳልሆነች ጠቋሚ ምልክቶች ምን እንደሆኑ እንዲገልጹ ማበረታታት
- ከተሳታፊዎች ጋር እነዚህ ጠቋሚ ምልክቶች እንዴት ከአምስቱ ቤተክርስቲያን ተከላ ደረጃዎች ጋር እንዴት እንደሚያያዙ ተወያዩ፡፡
- **እንዲህ ብለህ ጠይቅ "መቼ ነው ቤተክርስቲያኒቱ ጤናዋ መታወክ የጀመረው?"** ለዚህ መልስ ሲሰጡ ቤተክርስቲያኒቱ ስትተከል ጀምሮ ጤናማ እንዳልሆነች መገንዘባቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡
- **እንዲህ በል** "የዚህ ክፍለ ትምህርት ዋና አላማ የጤናማ ቤተክርስቲያን አስር መስፈርቶች ምንያህል አስፈላጊ እንደሆኑ እንድትረዱ እና እናንተም የምትተክሉት ቤተክርስቲያን በዚህ መሰረት ጤናማ በሆነ ምልኩ ትተክሉ ዘንድ እንዲያዘጋጃችሁ ነው፡፡ ከሆሳዕና ቤተክርስቲያን በተቃራኒ እናንተ የምትተክሉት ቤተክርስቲያን ጤናማ ካልሆነ አጀማመር የራቀ ሊሆን ይችላል፡፡"

**ጤናማ ያልሆነ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

ሆሳዕና የተባለው ቤተክርስቲየን ስመተከል የበቃው ከግጭት እና ጉዳት በመነሳት ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያመልኩ የነበሩ አባላት በሁለት መሪዎች ጎራ ይሰለፉሉ፡፡ አንዱ ቡድን ጡረታ የወጣውን መጋቢን የሚደግፉ ሲሆኑ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ አዲሱ መጋቢ የሚደግፉ ነበሩ፡፡ በዚህም የቤተክርስቲያኒቱ ዋና ጽህፈት ቤት ቤተክርስቲያኒቱ ለሁለት እንድትከፈል እና ሁለት አጥቢያ እንዲሆኑ ወሰነ፡፡



በጊዜ ሂደት አዲሱ መጋቢ ሆሳዕና የሚለውን የቤተክርስቲያን ስም በመያዝ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡ ታዲያ ይህ አዲስ ቤተክርሰቲያን ሲ የተባለን ሰው ዋና መጋቢ አድርጎ ሾመ፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ እርሱና የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች/ መሪዎች መስማማት ስላልቻሉ በፍጥነት ሌላ ቡድን ከቤተክርሰቲያኒቱ ተከፈለ፡፡በዚህ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የመረጡት እድሜአቸው ከ55 አመት በላይ የሆኑ ናቸው፤ በእርግጥ ጎልማሶች እና ወጣቶች በቤተክርሰቲያኒቱ አመራር ላይ እምብዛም እምነት አልነበራቸውም፡፡ ለዚህም ነበር ሆሳዕና ቤተክርስቲያን ከቀደመው አጥቢያ የተከፈለው፡፡ ለዚህም ይመስላል ሆሳዕና ቤተክርስቲያን ለውጥ ለመቀበል ዳተኛ የሆነችው፡፡ ከሌሳኛው ቤተክርስቲያን ጋር ሲነጻጸር፤ አብዛኛው አባል እድሜው የገፋ በመሆኑ ጊዜው የሚጠይቀውን ማንኛውንም ለውጥ እንዳይቀበሉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡

ታዲያ የመረጡት ወግ አጥባቂነት የተጠናወተው የአምልኮ ዘይቤ ዋጋ እያስከፈላቸው ይገኛል፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለውን የአምልኮ ስርአት የሚመስጣቸው በእድሜ የገፉት ብቻ በመሆናቸው ብዙ ህዝብ አጥተዋል፡፡ የዚህ ችግር ዋናው ማሳያ አንድ ሺህ ምዕመን የሚይዘው የማምለኪያ አዳራሽ በየሳምንቱ በአማካይ ሁለት መቶ ሰው ብቻ ነው የሚካፈልበት፡፡

የቤተክርስቲያኒቱ የገንዘብ አቅም በጣም የተመናመነ ከመሆኑ የተነሳ በቀዝቃዛው ወቅት እንኳን በኤሌክትሪክ የሚሰራውን የማሞቂያ መሳሪያ አይጠቀሙም፤ ለክርምት ብቻ ሳይሆን እጅግ ሙቀት በሚበዛበት ወቅትም ቢሆን እንኳን ይህን መሳሪያ ለመጠቀም አይደፍሩም፡፡ የዚህ ዋና ምክንያት ደግሞ የኤሌክትሪክ ክፍያውን ስለማይችሉት ነው፤ እንደውም ቤተክርስቲያኒቱ እዳ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ነገሩን የበለጠ የከፋ የሚያደርገው የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች አስራትና በኩራትን በተመለከተ ጠንካራ አቋም እና ትምህርት የላቸውም፡፡ በዚህም ላይ አዳዲስ አማኞችን

የሚከታተሉበት ስርአት እንኳን አሳበጁም። በትናንሽ ቡድኖች የተደራጁትም ቢሆኑ የቤተክርስቲያኒቱን ምዕመናን በሴቶችና እንዲህ በመሰሉ ቡድኖች ተደራጁ እንጂ ሌሎችን የሚስብ አልነበረም፤ እንደውም ቡድኑ በወንጌል ስርጭት የሚበዙ ሳይሆን በቀዬ አማኞች የተደራጀ ነው። የቤተክርስቲያኒቱ መታወቂያ የማያቋርጥ ጥል፣ መለያየት እና አለመተማመን ነው። ሆሳዕና ቤተክርስቲያ ራሱን ወደማደስ ከመድረሱ በፊት እንዲህ ባለ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነበር።

**አስሩ የጤናማ ቤተክርስቲያን ባህሪያት (5 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-**

- ከታች ያለውን ስዕላዊ መግለጫ ትምህርቱ እየተሰጠ ባለበት ወቅት ተራ በተራ በመሙላት እንዲከታተሉ አበረታታቸው።
- ከዚህም በተጨማሪ ትምህርቱን ማስታወሻ እየያዙ እንዲከታተሉ የተመቸ አድርግ




**እንዲህ በል "አስሩ መገለጫዎች አምስት ግብአት እና አምስት ተግባር የያዘ ነው"**

**ተሳታፊዎች አምስቱን ግብአቶች እና አምስቱን ተግባራት በተሰጠው ስዕላዊ መግለጫ ክፍት ቦታ እንዲሞሉ አበረታታቸው።**

እንዲህ በል "በአምስቱ ግብአቶች እንጀምር" ይህን ክፍል ስታስተምር ተሳታፊዎች አምስቱን ግብአቶች በስዕላዊው መግለጫ ላይ በተዘጋጀላቸው ስፍራ እንዲያሰፍረ እና ማስታወሻም እንዲይዙ አበረታታቸው፡፡

**አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ግብአቶች (20 ደቂቃ)**

1. **ግልጽ ራዕይ**

   **ፍቺ/ትርጉም፡-** ራዕይ ማለት እግዚአብሔር የእርሱን የመዋጀት አላማ በእናንተ እንዴት እንደሚፈጽም ሲመጣ ያለውን (የወደፊቱን) መመልከት ነው፡፡

   "እግዚአብሔር እንድንሰራው እና እንዲሆንለት የሚፈልገውን ቤተክርስቲያን አጥርታ እንድታይ የሚያግዝ፤ በዚህም የክርስቶስ አካል በአንድነት በእግዚአብሔር የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ታሳይ ዘንድ የሚያስችል ነው፡፡"

   እናንተ የምትተክሏት ቤተክርስቲያን ምን እንድትመስል እና ምን እንድትሰራ እግዚአብሔር ይፈልጋል? አዲስ ከተከላችኋት ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር የቤተክርስቲያኒቱን ራዕይ ወይንም እግዚአብሔር እዳቤተክርስቲያን ሲጠራችሁ እንድትሆኑለት እና እንድትሰሩለት የፈለገውን በአጭሩ ጽፋችሁ አስቀምጡ፡፡ ይህንንም ትኩረት ሰጥታችሁ የምትሰሩበት የአገልግሎታችሁ አቅጣጫ አድርጉት፡፡

2. **መሪነትን ማነቃቃት**

   **ፍቺ/ትርጉም፡-** ክርስቲያናዊ መሪነት እንደሚከተለው ሊፈታ ይችላል፤ "ክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር (ባህሪይ) የቀረጡ፤ ወዴት እንደሚሔዱ የሚያውቁ(ራዕይ) እና ተከታዮች ያሉአቸው ናቸው (ተጽዕኖ ፈጣሪ)፡፡" አንድን ሰው ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ስንሾም፤ የመሪነት ክህሎቱን ማሳደግ የሚችልበትን መንገድ አብሮ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

“መሪዎች ራዕይን የተረዱ እና ራዕዩን የሚኖሩ፣ ለማበረ ምዕመናቸው ራዕዩን በትክክል ማስተላለፍ የሚችሉ እና ቤተክርስቲያንን ለራዕዩ እውን መሆን እንደ አንድ አካል የሚያንቀሳቅሱ ናቸው”

እንዲህ በል "እስኪ ጳውሎስ እንዴት አድርጎ መሪዎችን እንዳሰለጠነ እና እንዳስታጠቀ እንመልከት።"

- አንድ ሰው 2ጢሞ 2፡2ን እንዲያነብ አድርግ

እንዲህ በል "ለጳውሎስ አዳዲስ መሪዎችን ለእያንዳንዱ አጥቢያ መሪነት ማብቃት መተኪያ የሌለው ጉዳይ ነበር፤ ምክንያቱም ቤተክርስቲያን እንድትጸና ይፈልግ ስለነበር፤ ይህንንም ነበር ያደረገው"

ሀ. ለመሪዎች ቦታ ይሰጥ ነበር፤ በስራው ላይም ይሾማቸው ነበር።

ለ. እነርሱን ለማዘጋጀት ቁርጠኛ ነበር።

ሐ. ያምናቸው ነበር።

3. **ወደአንድ ግብ የተንቀሳቀሰ አካል**

**ፍቺ/ትርጉም፡- የቤተክርስቲያኒቱ አባላት አንድ ሆነው፣ ጸጋቸውን ተጠቅመው ማህበረ-ምዕመኑን እና ማህበረሰቡን ለማገልገል ሲሰሩ ተንቀሳቃሽ አካል ይባላል።**

*“ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን”* 1ጴጥ 4፡10-11

**አምስቱ የትግበራ ደረጃዎች**

1. ሁሉንም ማህበረ ምዕመን ለማንቀሳቀስ መሪዎችን አዘጋጅ።
2. ስለ የጸጋ ስጦታ እና የባለአደራ መሪ ችሎታዎች አስተምር።
3. የእያንዳንዱን አባል ስጦታውን እና ሊሰማራበት የሚፈልገውን ስፍራ ለይ።

4. እያንዳንዱን ምዕመን በአገልግሎት ወይንም በግልጋሎት አካባቢ እንዲሰራ ሹም/ ቦታ ስጥ፡፡
5. የቤተክርስቲያኒቱ የተለያዩ የቤተክርስቲያን ሕይወት እንዴት እንደሚሰሩ እንቅስቃሴአቸውን በማጤን እና በአትኩሮት በመከታተል አስፈላጊውን ማሻሻያ ማድረግ፡፡

## 4. **እውነተኛ የግብአት ባለ አደራ**

**ፍቺ/ትርጉም** | ቤተክርስቲያን የመልካም ባለአደራ ምሳሌ በመሆን ማበረ ምዕመኗ ባላቸው ሃብት፣ ንብረት እና የሕይወት ግብአቶች (ጊዜ፣ ችሎታ/ስጦታ እና ድብቅ ሃብት) አንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ከልባቸው እንዲያኖሩት ማሳሳብ ያስፈልጋታል፡፡ በዚህም እነዚህን ግብአቶች እና ያላቸውን የገንዘብ ስጦታ በመጠቀም የእግዚአብሔርን መንግስት በቤተክርስቲያናቸውና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ግቡን ይመታ ዘንድ አዲጠቀሙበት ማነቃቃት፡፡

*"እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፥ ከፍሬህም ሁሉ በኵራት ጕተራህም እህልን ይሞላል፥ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች፡፡"* ምሳ 3፡9-10

## 5. **መልዕክትን እና አውድን ማዋደድ/ማዋሃድ**

**ፍቺ/ትርጉም** | ጤናማ ቤተክርስቲያን አውድን (መልክአምድራዊ መገኛን፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን፣ ባህልን እና የመሳሰሉትን…) ታሳቢ ታደርጋለች፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነው የወንጌላችን መልዕክት የማይለዋወጥ ሆኖ፤ እርሱን ለሌሎች የምንሰብክበት ስልት ግን ይለዋወጣል፡፡

*“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።”*
2ጢሞ 3፡16-17

## አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ተግባራት

1. <u>ወንጌል ስርጭትን የምታበረታታ</u>

ፍቺ/ትርጉም | “ቤተክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል <u>በቃል</u> እና <u>በተግባር</u> <u>በመንገርና</u> በመኖር ሰዎች የእግዚአብሔር መንግስት አካል ይሆኑ ዘንድ ሰውን ሁሉ ትጋብዛለች።”

*“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።”* ሐዋ 1፡8

*“ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር”* ሐዋ 2፡47

- የኢንግል መስኪያ
- ቀን መቁጠሪያ እና የተግባር መቆጣጠሪያ፤ እነዚህ ዳሴዎች ቤተክርስቲያን በእርግጥ ለወንጌል ስርጭት የተሰጠችና ቁርጠኛ የሆነች መሆን አለመሆኗን እንድናረጋግጥ ይረዱናል።
  “ታላቁ ተልዕኮ እንደየሁኔታው እንድንቀበለው በአማራጭነት የተቀመጠ ሳይሆን፤ እንድንታዘዘው የተደነገገ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው።”

2. <u>ሁሉን አቀፍ የደቀመዝሙርነት ስልጠና</u>

**ፍቺ/ትርጉም፡-** ቤተክርስቲያን ሰዎች ኢየሱስን ጥርት አድርገው እንዲያዩትና ስለሕይወታቸው የእርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ እንዲያውቁ ታግዛለች፤ ይህም በሁሉም የሕይወት ዘርፍ ኢየሱስን እንዲከተሉ ትጥቅ ይሆናቸዋል፡፡”

*“ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ፡፡ ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን፡፡”* 1ጴጥ 3፡18

*“በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር፡፡”* ሐዋ 2፡42

**የደቀመዝሙርነት አራቱ ቁልፍ ቃላት**

1. ተግባር.
2. ባህሪ.
3. የወንጌሉ ይዘት.
4. መስጠት.

## 3. ግልጋሎት

**ፍቺ/ትርጉም፡-** ቤተክርስቲያን የህዝብን ፍላጎት በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እየደረሰች የእርሱ ደቀመዛሙርት ይሆኑ ዘንድ ትጋብዛለች፡፡

*“ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ፡፡ መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር፡፡ ... እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፡፡”* ሐዋ 2፡45፣47

**በወንጌል ስርጭት እና በአገልግሎት መካከል ሶስት አይነት ግንኙነቶች አሉ**

1. አገልግሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ ውጤት ሲወሰድ፡-ጌታን መቀበላችን ለሌሎች ወገኖቻችን ፍላጎት ይሞላ ዘንድ ንቁ ያደርገናል፡፡
2. አገልግሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ ድልድይ ሲሆን፡- ሌሎችን ወንጌልን በቀጥታ ለመስማት ፈቃደኛ ይሆኑ ዘንድ ቀድሞ እነርሱን ማገልገል፡፡
3. አገልገሎት የወንጌል ስርጭት ያጅባል ፡- ሌሎችን በማገልገል ሂደት ውስጥ ስለኢየሱስ መናገር፡፡

### 4. ህብረት

**ፍቺ/ትርጉም | ማህበረ ምዕመኑ አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም፤ የክርስቶስን ፍቅር እና ርህራሄ ማሳየት፡፡**

"…በኅብረት…ይተጉ ነበር። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ … በደስታና በጥሩ ልብ…" ሐዋ 2፡42፣44፣46

### 5. አምልኮ

**ፍቺ/ትርጉም፡- ቤተክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ስትሰበሰብ ልትፈጽም የምትችለው አንድ ጉዳይ እግዚአብሔር አብን ማምለክ፣ በደሳችንን መናዘዝ፣ አድናቆታችንን መግለጽ፤ ከዚህም በተጨማሪ ለጸሎት እና ለአገልግሎት ራስን መስየት ነው፡፡**

*"ከሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር፡፡ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፡፡"* ሐዋ 2፡42፣47

የጥናት ቡድኖች ተግባር፡- አስታውሳለሁ የዛን ጊዜ…(10 ደቂቃ)

**ለአሰልጣኙ የቀረበ ማስታወሻ፡- የዚህ ተግባራዊ ልምምድ ዋናው ዓላማ ሰልጣኞች ቀድሞ የነበራቸውን ልምድ በዚህ ትምህርት ካገኙት አዲስ ዕውቀት ጋር በማነጻጸር አሳባቸውን እንዲገልጡ እድል መስጠት ነው፡፡**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- **ተሳታፊዎችን ሶስት ወይንም አራት ሰው በያዘ ትናንሽ ቡድን በመክፈል፤ እያንዳንዱ ቡድን ስለጤናማ ስለሆነ እና ጤናማ ስላልሆነ ቤተክርስቲያን ያላቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ አበረታታ፡፡ እያንዳዱን በትናንሽ ቡድኖች ተሳታፊ የሆነን ተሳታፊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሃረግ እንዲሞሉ ጠይቃቸው፡- አስታውሳለሁ የዚያን ጊዜ (አንድ የተፈጠረን ጉዳይ ጥራ)፤ አንዲህ (የተሰማህን ስሜት ግለጥ)**

እንዲሰማኝ አድርጓል፤ እናም (በጊዜው የተወሰደን እርምጃ ልምድ)፣ ምክንያቱም(ለምን ይህ እርምጃ ተወሰደ)።

የጤናማ ቤተክርስቲያን ልምምድ ምሳሌ፡- አስታውሳለሁ መጋቢዬ እኔን ደቀመዝሙር ለማድረግ የሰጠኝን ሰፊ ጊዜ፤ እንዲህ ሲያደርግ ለእርሱም ሆነ ለቤተክርስቲያን በጣም አስፈላጊ እንደሆንኩ ነበር የተሰማኝ። ለዚህም ነው ወደጌታ የሚመጡ ሰዎችን ለማስተማር የመረጥኩት እነርሱም እንደኔ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ እንደሆኑ እንዲሰማቸው ስለምፈልግ።

ጤናማ ያልሆነ ቤተክርስቲያን ምሳሌ፡- አስታውሳለው አንድ ቀን በምኖርበት አካባቢ የሚገኝ አንድ ቤተክርስቲያን ልካፈል ሄድኩ፤ እዚያ እንደገባሁ ማንም ሰው ሰላም ያለኝ ሰው አልነበረም፤ በዚህም ማንም ስለኔ ግድ እንደሌለው ተሰማኝ። በዚህም ደግሜ ወደዛ ቤተክርስቲያን ዝር ሳልል ወስኜ ወጣሁ። ምክንያቱም ስለእኔ ግድ የሚላቸው ወንድሞች እና እህቶች ያሉበት ቤተክርስቲያን በገኘት ስለምፈልግ።

ይህን ምሳሌ በቀላሉ እንዲህ አቅርበናል፡- አስታውሳለሁ አንድ ወቅት____________________ ________________________________________________፤ እዚያም ስሄድ አቀባባላቸው ________________________________እንዲሰማኝ አደረገኝ፤ ከዚህም የተነሳ ____________________________________።

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- በየቡድኑ የታቀፉ ተሳታፊዎች እያንዳንዳቸው ያላቸውን ልምድ ለቡድናቸው እንዲያካፍሉ፤ ከዚያም የእነርሱ ልምድ በዚህ ክፍለ ትምህርት ከተማሩት ከአስሩ የጤናማ ቤተክርስቲያን መገለጫዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ እንዲወያዩ አበረታታቸው።

- በመጨረሻም ይህን ክፍለትምህርት እንዲህ ብለህ አጠናቅ "በእነዚህ አስራ ሁለት የስልጠና ሞጁሎች እነዚህን አስር የጤናማ ቤተክርስቲያን መገለጫዎች እንዴት እናንተ በምትተክሉት ቤተክርስቲያን ላይ እንደምትተገብሯት ትማራላችሁ፤ በመጨረሻም የአዲስ እና ጤናማ ቤተክርስቲያን ውልደትን እናበስራለን፡፡"

# ክፍለትምህርት 2

# ጤናማ የቤተክርስቲያን ተከላ

# አገልጋይ ምንድን ነው? (60 ደቂቃ)

## አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ጠቋሚ ምልክቶች (40 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ:- እንዲህ በል "ጤናማ ቤተክርስቲያን ለመትከል፤ ራሱ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ጤናማ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት አምስቱን የጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ጠቋሚ ባህሪያት እንመለከታለን፡፡"

- ስለዚህ ጉዳይ በማስተማር ላይ ሳለህ ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ስዕላዊ መግለጫ እንዲሞሉ አበረታታቸው፡፡
- "በእግዚአብሔር የተጠራ" ከሚለው ጀምር ከዚያም ወደቀኝ ዙሪያውን ተራ በተራ ፈጽም፡፡




## ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚያበቃ በራስ መተማመን እንዳለኝ ለማወቅ የሚረዳ ግምገማ (20 ደቂቃ)፡፡

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- የዚህ ክፍለትምህርት ዓላማ ተሳታፊዎች ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ልምድ አሁን ከሚማሩት አምስቱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ማሳያ ጋር በማስተያየት ያስቡ ዘንድ ነው፡፡

- ተሳታፊዎች ከዚህ በታች ያለውን ራስን የመገምገሚያ እና በራስ መተማመን ለማዳበር የሚረዳ እቅድ ማዘጋጃ ቅጽ እንዲሞሉ አበረታታ፡፡

የሚከተለውን ራስን የመገምገሚያ ቅጽ የእናንተ በራስ መተማመን ምን አይነት ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ እያንዳንዱ አርፍተነገር እንዴት እንደሚገልጻችሁ አስረዱ፡፡

ከዚህ ቀደም እንደቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ በነበረኝ ባህሪና ልምድ…

1. እምነቴን በቋሚነት በተግባር አውያስሁ ደግሞም ጠንካራውን የጥሞና ጊዜዬን እያስኩ እገኛስሁ፡፡

2. ያስምንም የሌላ ሰው ቁጥጥር በራስ ተነሳሽነት ስራዎችን ማከናወን እችስላሁ

3. የትዳር አጋሬን ድጋፍ አግኝቻስሁ

4. ጤናማ ቤተክርስቲያን በመትከል ረገድ ምን መደረግ እንዳስበት እና ውጤቱ ምን እንደሚሆን ጥርት ባስ ሁኔታ በህሊናዬ ስዕሉ ይታየኛል፡፡

5. ከላይ በህሊናዬ ያየሁትን ስዕል መፈጸም የሚያስችስኝን ቡድን ማዋቀር የምችልበት አቅም አስኝ፡፡

6. ከቤተክርስቲያን ተከላ አውድ ጋር በሚገባ ተዋህጃስሁ፡፡

7. ከማህበረሰቡ ጋር መልካም የሚባል ህብረት እገነባስሁ

8. ከሰዎችና ከሁኔታዎች ጋር ያስኝ መስተጋብር ግትር ከመሆን ይልቅ ከሁኔታዎች ጋር ስመዛመድ የተመቸሁ እሆናስሁ፡፡

9. አዲስ የሚተከስው ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ እድገት እንዲኖረው ምሪትን እሰጣስሁ

10. አዲስ የሚተከስው ቤተክርስተያን ውጤታማ የሆነ ድርጅት (አደረጃጀት) እንዲሆን ማድረግ እችላስሁ

11. የቤተክርስቲያንን አባላት በመጠቀም ቤተክርስቲያን በቁጥር እንድታድግ ምሪትን እሰጣሁ

12. ህብረትን ስማጠንከር የሚረዳ ትረጉም ያስው እና በቁጥር ከፍ ያስ እድል እፈጥራስሁ

13. ግጭቶችን ጤናማ በሆነ መንገድ መፍታት እችላስሁ

14. ሌሎች በአገልግሎት እንዲሳተፉ አደርጋስሁ

15. ምዕመናን የጸጋ ስጦታቸውን እንዲለዩ እና እንዲጠቀሙ አግዛለሁ

## በራስ መተማመንን ለመገንባት የሚረዳ እቅድ

1. አሁን ባለሁበት ሁኔታ ምንድን ነው ቁጥር አንድ በራስ መተማመኔን ልገነባበት የሚያስፈልገኝ የሕይወት ዘርፍ?

2. ከላይ የገለጥኩትን የሕይወት ዘርፍ ለማሻሻል በፍጥነት ልወስድ የምችለው እርምጃ ምንድን ነው?

3. ከላይ ከሞላኸው ቅጽ ከፍተኛ በራስ መተማመን አለኝ ብለህ ያመንክበትን በሚገባ አስተውል ምክንያቱም እነዚያ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይነትህ ዋና ዋና ጠንካራ ጎኖች ናቸው:: ከቤተክርስቲያን ተከላ ጎን ለጎን ነው እንዴት እነዚህን ጠንካራ ጎኖች በበለጠ ለማዳበር ምን አይነት እርምጃ ትወስዳለህ?

4. ማንን ነው በፀሎት እንዲረዳኝ፣ በግልጽነት እያንዳንዱን የሕይወት ውጣ ውረዱን የማዋየው እና በራስ መተማመኔን በበለጠ ለማዳበር እንዲረዳኝ የምመርጠው?

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- ተሳታፊዎችን ሶስት ወይንም አራት ሰው በሚይዝ ቡድን በመክፈል ከዚህ ትምህርት ስለራሳቸው ምን እንደተማሩ እና የመገምገሚያ ቅጹን ሞልተው ባገኙት ውጤትና በተማሩት መሰረት ምን አይነት እርምጃ ለመውሰድ እንደወሰኑ ለቡድናቸው እንዲያካፍሉ አበረታታቸው፡፡
- ከዚያም አንዱ ቡድን ለሌላው እንዲጸልዩ በማድረግ የትምህርት ጊዜውን አጠናቅ፡፡

ተለዋጭ የትግበራ መምሪያ፡-

- ከታች ያለውን ራስን የመገምገሚያ ቅጽ ውጤት ማሳወቂያ ቅጽን በመጠቀም ከጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ተምሳሌት ጋር ልምዳቸውን በማዛመድ የጠለቀ መረዳት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚያበቃ በራስ መተማመን እንዳለኝ ለማወቅ የሚረዳ ግምገማ የውጤት ማሳያ ቅጽ

| ዝቅተኛ በራስ መተማመን | በቂ በራስ መተማመን | ከፍተኛ በራስ መተማመን | ድምር ውጤት |
|---|---|---|---|
| ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ዝቅተኛ በራስ መተማመን እንዳሳችሁ የመዘገባችሁትን ጥያቄ ተራ ቁጥር መዝግቡ። ለምሳሌ "ዝቅተኛ በራስ መተማመን" 1፣6፣7 | ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ በቂ በራስ መተማመን እንዳሳችሁ የመዘገባችሁትን ጥያቄ ተራ ቁጥር መዝግቡ። ለምሳሌ "በቂ በራስ መተማመን" 2፣8፣10 | ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ ከፍተኛ በራስ መተማመን እንዳሳችሁ የመዘገባችሁትን ጥያቄ ተራ ቁጥር መዝግቡ። ለምሳሌ "ከፍተኛ በራስ መተማመን" 3፣11፣15 | |
| | | | |
| ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ "ዝቅተኛ በራስ መተማመን" ብሳችሁ የሞሳችሁትን ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት አቅርቡ። ለምሳሌ ለሶስት ጥያቄዎች መልሳችሁ "ዝቅተኛ በራስ መተማመን የሚል ከሆነ" ቁጥር 3ን ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ አስፍር። | ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ "በቂ በራስ መተማመን" ብሳችሁ የሞሳችሁትን ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት አቅርቡና ያንን ውጤት በ2 አባዙት። ለምሳሌ ለሶስት ጥያቄዎች መልሳችሁ "በቂ በራስ መተማመን የሚል ከሆነ" 3 ሲባዛ 2 ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ አስፍር 6ን አስፍሩ። | ከዚህ በታች ባለው ክፍት ቦታ "ከፍተኛ በራስ መተማመን" ብሳችሁ የሞሳችሁትን ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት አቅርቡና ያንን ውጤት በ3 አባዙት። ለምሳሌ ለሶስት ጥያቄዎች መልሳችሁ "ከፍተኛ በራስ መተማመን የሚል ከሆነ" 3 ሲባዛ 3 ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ 9ን አስፍሩ። | ከዚህ በታች ባለው ሳጥን ውስጥ ደግሞ የሶስቱን ማለትም የዝቅተኛ፣ በቂ እና መካከለኛ በራስ መተማመን እንዳሳችሁ ያሰፈራችሁትን ውጤት ድምር አስቀምጡ፤ ለምሳሌ የዝቅተኛ 3፣ በቂ 6 እና ከፍተኛ 9 በመሆኑም ጠቅላላ ድምር ውጤታችሁ 3+6+9 = 18 |

የውጤት መገኛ ርቀት፡

የጠቅላላው ድምር ዝቅተኛ በራስ መተማመን ውጤት፡- 15-25

የጠቅላላው ድምር ውጤት ለበቂ በራስ መተማመን፡- 26-35

የጠቅላላው ድምር ውጤት ለከፍተኛ በራስ መተማመን፡- 36-46

- ለሶስቱም በራስ መተማመን አይነቶች የመለሳኋቸው መልሶች አንድ ላይ አድርጋችሁ ስትመለከቷቸው እርስ በእርስ የሚገናኙበት ሂደት አለ?
- ለሶስቱም በራስ መተማመን አይነቶች የሰጠኸውን ምላሽ ካስተዋልክ በኋላ እንዴት የሶስቱ በራስ መተማመን አይነት ውጤት እንዴት ለጠቅላላው ውጤት አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ? ይህ ውጤት ቤተክርስቲያን የመትከል ዝግጅትህ ምን እንደሚመስል በቂ እይታ ሰጥቶሃል?

ይህ ራስን የመገምገሚያ ቅጽ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ብቁ መሆን አለመሆኑን/አለመሆኗን ለመለካት የሚረዳ የመገምገሚያ መሳሪያ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ መገምገሚያ የቤተክርስቲያ ተከላ ስራችንን ብቃት የሚገመግም መሳሪያ አይደለም፡፡ ይልቁንም ራስን ለመገምገምና ከሌሎች የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች እና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትን ከሚያሳልጥ መሪ፣ የማማከርና ድጋፍ አገልጋይ ወይንም ስራን የሚቆጣጠርና ከሚያሳልጥን አገልጋይ ጋር መልካም የሚባል የውይይት በር የሚከፍት ቅጽ ነው፡፡



# ክፍለ ትምህርት 3

# "የመጨረሻ" አሳብ፡

# እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል? (60 ደቂቃ)

**"የመጨረሻ" አሳብ ምንድን ነው? (10 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ይህን ጥያቄ አቅርብ ""የመጨረሻ" አሳብ ምንድን ነው?"**

"የመጨረሻ" ማለት በዚህ ክፍለ ትምህርት የመጨረሻው ውጤት እግዚአብሔር አገር፣ ክልል፣ ከተማ፣ መንደር ወይንም ጎረቤት የሚያስበው የልቡ አሳብ ተከውኖ ማየት ነው። ለዚህም "የመጨረሻ" የሚለውን ቃል መጠቀም የፈለግነው። በፊደል መሰየም ቢያስፈልግ "ፐ" ወይንም "Z" ወይንም ኦሜጋ የሚባለውን የግሪክ የመጨረሻ ፊደል መጠቀም ይቻላል።

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከዚህ በታች ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተሳታፊዎች እንዲያነቡና ባነበቡት ክፍል ላይ አሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታቸው።

**አንብቡ፡-** ኢሳ 11:9፤ 65:12-25፤ ራእ 21:1-4፣ 22-27፤ 22:1-5

**አሳባችሁን ግለጹ፡-**

- እንዴት ነው እነዚህ ክፍሎች "የመጨረሻውን ፍልሚያ" የሚገልጡት (እግዚአብሔር በመጨረሻ ሊያየው የሚፈልገው)?

- ሲመጣ ስላለው አዲስ ምድር ትኩረት ሳያደርጉ በሰማያዊ ተስፋ ላይ ብቻ ትኩረትን ማድረግ ምን አይነት አደጋ ያስከትላል?

**አንብብ፡-**

ማር 13:10 ማቴ 24:14 ዮሐ 3:16 1

ጢሞ 2:3-4 ሉቃ 24:45-47 2 ጴጥ 3:9

ቆላ 1:6 2 ቆሮ 5:9



**አሳባችሁን ግለጡ፡-**

- እነዚህ ክፍሎች እግዚአብሔር አለምን በልጁ ወንጌል ለመድረስ ስላለው እቅድ ምን ይነግሩናል?
- እግዚአብሔር የልቡን መሻት ለማግኘት ከሚጠቀምባቸው መንገዶች መካከል በከፊል የትኞቹ ናቸው?
- እግዚአብሔር የልቡን መሻት ለማግኘት ከሚጠቀምባቸው መንገዶች መካከል ዋናው መንገድ የትኛው ነው?
- እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመን እየተጠቀመበት ያለ ውጤታማ መንገድ ሊሆን የሚችል አማራጭ አለ?

**አንብብ፡-**

ማቴ 28:18-20 ሐዋ 1:8 ኤፌ 3:10

**አሳባችሁን ግለጡ፡-**

- ከላይ ያነሳናቸው ክፍሎች የእግዚአብሔርን የልብ አሳብ በመፈጸሙ ረገድ የእኛ ድርሻ ምን እንደሆነ ይነግሩናል?

### "መጨረሻ" ላይ ለመድረስ ሲወሰዱ የሚገባ አንዳንድ ወሳኝ እርምጃዎች (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-**

- ተሳታፊዎችን በሶስት ወይንም አራት ቡድን ከፋፍሏቸው
- እያንዳንዳቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ከዚህ በታች ከምናገኛቸው አምስት ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የሚዛመዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዲያነብቡ በማድረግ በቡድናቸው እንዲወያዩበት ማበረታታት፡፡
- ከአስር ደቂቃ የቡድን ውይይት በኃላ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ደቂቃ በመስጠት ዋና ዋና የሚሏቸውን ነጥቦች በአጭሩ ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ፡፡

**ሀ. ጸሎት** 2ዜና 7፡14፤ ማቴ 9፡38

የ"መጨረሻ" ብለን ከላይ ያነሳነውን እግዚአብሔር ለመላው ዓለም ያለውን አሳብ ለማሳካት የጸሎት ርእሳችን ምን ሲሆን ይገባል?

**ለ. ፍቅርና አንድነት** ዮሐ 13፡35፤ 17፡20-23

"መጨረሻ"ን ከግብ ለማድረስ የፍቅርና የአንድነት አስፈላጊነት ምን ሲሆን ይችላል?

**መ. ራዕይ** ዮሐ 3፡16፤ 1ዮሐ 2፡2፤ ማቴ 9፡37

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ራዕይ ምን ይነግሩናል?

**ሰ. ወንጌል ስርጭት** ሮሜ 10፡14-15

እንዴት ነው በአካባቢያችን ላሉ ሰዎች ወንጌልን ለመስበክ የሚመች አጋጣሚን የምናገኘው?

እንዴት አማኝ ወገኖች ከእነርሱ ጋር አብረው ከሚያመልኩ አማኞች ባሻገር ያሉትን ወገኖችን መድረስ የሚችሉት?

**ረ. ቤተክርስቲያን ተከላ ኤፌ 3፡8-11፤ ኤፌ 4፡11-13**

እግዚአብሔር ህዝቡ ምን እንዲከውኑለት ይፈልጋል? አንድ አዲስ ቤተክርስቲያን ተተከለ ማለት ሰዎች በዚያች ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚኖሩና የክርስቶስን ወንጌል ሳይሰሙ ይኖሩ የነበሩ ማህበረሰቦች ከዚህች አጥቢያ ወንጌልን የመስማት እድላቸው ሰፋ እንደማለት ነው፡፡ እንዲህ እንዲሆን የሚያደርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? እንዲህ ያለ (በአንድ ስፍራ ከተተከለ ቤተክርስቲያን የተነሳ የወንጌል መስፋፋት) አጋጣሚ የምታውቁ እንደሆነ ለቡድናችሁ እንዴት በዚህ መልክ ወንጌል እንደተስፋፋ ተናገሩና ተወያዩበት፡፡

**"የመጨረሻ" አስተሳሰብ ውጤቱ በ"መጨረሻ" ድርጊት ይታወቃል (10 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "ከ"መጨረሻ" አሳብ የሚገኘው ውጤት "የመጨረሻ" <u>እቅድ</u> እና "የመጨረሻ" <u>ስጋስነት</u> ነው" ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩባቸው፡፡

1. የቤተክርስቲያን ተከላ እውን እንዲሆን መመለስ የሚገባቸው ወሳኝ ጥያቄወች የትኞቹ ናቸው?

2. አንዴት ቤተክርስቲያን አዲስ አጥቢያ ስመትከል ስታስብ ምን አይነት እቅድ ቀድማ ማዘጋጀት ይኖርባታል?

**ለሞጁል 2 የሚረዳ የትግበራ አቅድ፡- የእናንተ "የመጨረሻ" እቅድ**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከታች የቀረበውን የቤት ስራ (አሳይንመንት) ከተሳታፊዎች ጋር አንብቡ፡፡
- የዚህ የቤት ስራ ውጤት በሞጁል 2 ትምህርት ወቅት ለቡድን የሚቀርብ እንደሆነ ንገራቸው፡፡
- በቤትስራው ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ በቂ ጊዜ ውሰድ፡፡

**የቤት ስራ (አሳድንመንት)**

1. ቤተክርስቲያን ለመትከል ያቀዳችሁበትን ስፍራ ካርታ በማዘጋጀት በዚህ ስፍራ የሚገኙ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ሊኖራቸው ከሚችል የቦታ ስፋት ግምት ጋር በማቅረብ፤ በዚያ ሊኖር የሚችለውን የህዝብ ብዛት በማወቅ" ቤተክርስቲያን የምትተከልበትን ከተማ እና ልዩ ስፍራ መወሰን፡፡

አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች እንዳስቀመጡት ቤተክርስቲያን በበቂ ሁኔታ አለ ለማለት ወይንም ቤተክርስቲያን ተከላ በአንድ አካባቢ "ፍላጎትን አሟልቷል" ለማለት አንድ ቤተክርስቲያን ለአንድ ሺህ ሰው መድረስ ሲችል ብቻ ነው፡፡ለአንድ ሺህ ሰው አንድ ቤተክርስቲያን በሚለው ከተስማማን እናንተ ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰባችት ከተማና ልዩ ስፍራ ምን ያህል ቤተክርስቲያናት መተከል ይገባቸዋል?

2. ስለቤተክርስቲያን ተከላ ስታስብ እቅድህን ሙሉ ለማድረግ ጸሎትን፣ አንድነት እና ፍቅርን፣ ራእይን፣ ወንጌል ስርጭትን እና የቤተክርስቲያን ተከላን አካቶ ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ የመነሻ የሚሆንን አሳብ ጻፍና ለአማካሪና ደጋፊህ አሳብህን አካፍል፡፡

3. ስለ ቀርብ አካባቢህ፣ መንደርህ፣ ከተማ እና ክልል፣ ወይንም አገር በማሰብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይህን ከግምት ውስጥ አስገባ፡-

- እግዚአብሔር ለ_____________________ (ቤተክርስቲያን መትከል ያሰብከበትን ከተማ፣ መንደር፣ ወይንም የቀርብ አካባቢ ስም አስገባ) ምን ይፈልጋል፡፡
- በዚህ አካባቢ እንዲሆኑ የምትፈልጋቸውን ሶስት "የመጨረሻ" ውጤቶች ጻፍ፡፡

**ወደ "መጨረሻ መስጠት" መድረስ** (10 **ደቂቃ**)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**



- ተሳታፊዎች 2ቆሮ 8፡7፤ 2ቆሮ 9፡6-7ን ያንብቡ፡፡

- ከዚያም ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ተወያዩበት።

**ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚያስፈልገው በጀት በለጠት አለመለጠቱን በምን እርግጠኛ ልንሆን እንችላለን?**

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- ከዚህ በታች የተቀመጠውን ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚያስፈልግን በጀት እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል እና ለመሰብሰብ የሚረዱ መንገዶች የተገለጹበትን መርህ ለተሳታፊዎች አስረዳ።
- ተሳታፊዎችም በተቀመጠላቸው ቦታ ላይ ተገቢ በሆነ መጠን እንዲጽፉ አበረታታ።

እንዲህ በል፤ "ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚሆን ገቢን ለማሰባሰብ የሚረዱ ሁለት ጠቃሚ ጽንሰ አሳቦች አሉ"

ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚሆን ገቢ የምንሰበስብባቸው ሁለቱ ጽንሰ አሳቦች

1. <u>እግዚአብሔርን ማመን</u>

2. <u>መርካት</u>

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- ተሳታፊዎች ፊሊ 4፡6-7፣ 11-13፣ 19 ን ያንብቡና በዚህ ክፍል ከምናገኛቸው ሁለት መርሆች ጋር ያላቸውን መስተጋብር እንዲወያዩ ጥቂት ጊዜ ይውሰዱ።
- ከዚያም ለተሳታፊዎቹ ከዚህ በታች ያሉትን ለቤተክርስቲያን ተከላ ገቢ የምናሰባስብባቸውን መንገዶች አብራራ።

አንብብ፡-

ፊሊ 4፡6-7፤ 4፡11-13፣ 4፡19

## አዲስ የሚተከሉን ቤተክርስቲያን በገንዘብ ለመደገፍ የሚረዱ መንገዶች

1. ከእናት ቤተክርስቲያን የሚገኝ ድጋፍ
2. ከእምነት ተቋም፣ ከተልዕኮ፣ ወይንም ድርጅት የሚገኝ ድጋፍ
3. ለዚህ ዓላማ ከተለዩ ደጋፊ ቡድኖች
4. ከኢንቨስተሮች፣ ወዳጅ እና ዘመዶች
5. ንብረት በመሸጥ ከሚገኝ ገቢ
6. ቤተሰብ ውስጥ ሁለት ሰራተኛ ካለ የአንዱን ሰው ደሞዝ ሙሉ ለሙሉ በመስጠት
7. ጥምር-ሙያ አገልግሎት

# ክፍለ ትምህርት 4

# የቤተክርስቲያን ተከላ ዙር

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከታች የቀረበውን የቤተክርስቲያን ተከላ ዙር ስዕላዊ መግለጫን በመጠቀም ስለቤተክርስቲያን ተከላ ዙር ጠቅለል ያለ ማብራሪያ ስጥ፡፡

የቤተክርስቲያን ተከላ ዙር (5 ደቂቃ)




**በትናንሽ ቡድን የሚደረግ ተግባራዊ ልምምድ** (25 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ተሳታፊዎችን በሰባት በመክፈል (አንድ ቡድን ለአንድ ክፍል (phase)) በመስጠት ሁሉም የራሳቸውን አንድ ክፍል እንዲያስቡ አበረታታ
- እያንዳንዱ ቡድን እነርሱ ከያዙት ክፍል ጋር የሚዛመዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለሁሉም ቡድን እንዲያነብቡ አበረታታቸው፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን የሚጠበቅበትን ክፍል (phase) ከግብ ለማድረስ "ተግባራዊ ልምምድ" እና "ቁልፍ ጉዳዮችን" ለማሳካት የሚችሉትን ያህል የተግበራ እቅድ እንዲያወጡ አበረታታ፡፡

**ክፍል (phase) 1፡- ጸሎት** (ሉቃ 10፡2፤ ኤፌ 6፡18-19፤ ቆላ 4፡2-4)

**ተግባራዊ ልምምድ፡-**

- በጸሎት ጀምር
- ከየትኛው ቡድን ጋር ወንጌል ስርጭትን እና የቤተክርስቲያን ተከላን እንደምታከናውን ጠቁም
- ለራስህና ለሚረዱህ ሰዎች ጸልይ

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- የት ነው የእኔ መኸር ያለው? እግዚአብሔር ከዚህ የመኸር ስፍራዬ ምን ይፈልጋል?
- እግዚአብሔር ለእኔ ለሰጠው ጥሪ እና ራዕይ በምን መልኩ ለሌሎች ከሰጠው ጥሪ እና ራዕይ ይለያል?
- ማነው የሚረዳኝ?
- ስለማን መጸለይ ይገባኛል? ምንስ ነው የጸሎቴ ርእስ?
- እግዚአብሔር በውስጤ ያስቀመጠውን ጥሪ በተመለከተ ምን እንድለምነው ይፈልጋል?

**ክፍል (phase) 2፡- ወንጌል ስርጭት** (1ቆሮ 9፡19-23፤ ሐዋ 1፡8)

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- ወሳኝ የሆኑ መሪዎችን በማግኘት ከእነርሱ ጋር ሕብረትን ገንባ።
- የጠፉትን በወንጌል ድረስ።
- በወንጌል ከደረስካቸው ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀምር።
- ከአዳዲስ አማኞች ጋር አንተ በጀመርክበት መንገድ ማገልገል ይጀምሩ ዘንድ መንገዱን አሳይ።

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- ምን አይነት የወንጌል ስርጭት ስልት ነው እኛ ያስቀመጥነውን ግብ ለመምታት የሚረዳን?
- እንዴት ነው ቁልፍ ከሆኑ ሰዎች ጋር መተዋወቅ የምንችለው? እነማንስ ናቸው?
- እንዴት ነው የምናገኛቸው?
- እንዴት ነው አዳዲስ አማኞች ጓደኞቻቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በወንጌል እንዲደርሱ የምናስለጥናቸው?
- እንዴትስ አድርገን የአዲስ አማኙን ጓደኞች እንተዋወቃለን እንዴትስ አድርገን እነርሱን በወንጌል እንደርሳለን?

**ክፍል (phase) 3፡- ደቀመዝሙር ማድረግ** (1ተሰ 5፡11፤ ማቴ 28፡18-20)

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- አዳዲስ አማኞችን ደቀመዝሙር ማድረግ
- እየተነሱ ያሉ አዳዲስ መሪዎችን በማማከርና ድጋፍ ማገልገል
- ለጌታ በመታዘዝ እና በመስጠት እንዴት መኖር እንደሚቻል ማስተማር
- አማኞች ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ ማበረታታት
- አዳዲስ አማኞች ክርስቶስን ይታዘዙ ዘንድ ማስተማር

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- እንዴት አንድን የሰዎች ስብስብ ደቀመዝሙር ማድረግ እና ማሳደግ ይቻላል?
- እንዴትስ መሪነትን ሞዴል ሆኖ ማቅረብ ይቻላል?

**ክፍል (phase) 4፡- መሰባሰብ** (ዕብ 10፡24-25)

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- የጓደኞችን ቁርኝት በመጠቀም የወንጌል ስርጭትን ጥረት ማስፋት

- የቡድን ጥናትን በማብዛት እና እያንዳንዱ የጥናት ቡድን እንዴት ሌላ የጥናት ቡድን እንዲመሰርት ማበረታታት
- በቋሚነት የሚደረግ የአምልኮ መርሃግብርን መጀመር

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- እንዴት አዳዲስ የቡድን ጥናት መሪዎች ሰልጥነው ለስራ ይሰማራሉ?
- መቼ ነው አዳዲስ አማኞችን ማጥመቅ የሚገባን? መቼ እና ማን ነው የጌታ እራት አዘጋጅቶ የሚሰጣቸው?
- ከአማኞች ጋር የጠበቀ ህብረት እንዴት መመስረት እንችላለን? እንዴትስ አዳዲስ አማኞች ወደ ህብረታችን እናመጣለን?
- ለመሰባሰብ ስፍራን እንዴት እንመርጣለን ወይንም የት እንሰባሰባለን? እንዴትስ ነው ሰዎች የምንጋብዘው?
- ያሰብነውን ዓላማ ለማሳካት ምን አይነት መንገድ እንጠቀማለን?
- ምን አይነት የአምልኮ ዘይቤ እንጠቀማለን?

**ክፍል (phase) 5፡- መሪዎችን ማብቃት** (2ጢሞ 2፡2)

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ መሪዎችን ማንነት የሚገልጥ ቀጽ አዘጋጅ
- የአባላቱን በሙሉ የጸጋ ስጦታ ፈልግ ደግሞም በጽሑፍ አስፍር
- የቡድን መሪዎችን አሰልጥን
- መሪዎችን በመሾም እና ስፍራ በመስጠት አሰማራ
- ለአገልግሎቱ ይሆናል ብለህ ያሰብከውን አደረጃጀት እና የአገልግሎት ሹመት ስፍራ አደራጅ
- መርዳት የሚገባህን ሁሉ ታደርግላቸው ዘንድ የመሪዎችን አገልግሎት በደህና ተከተል

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- እንዴት ነው አዳዲስ አማኞች ያላቸውን የጸጋ ስጦታ እንዲለዩ የምናስችለው? ማንስ ነው የሚያሰለጥናቸው?
- ስልጠና የሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው? የት እና እንዴት ስልጠናው ሊሰጥ ይችላል?
- እነማንስ ናቸው ነገሩን ለመከወን አቅም ያላቸው መሪዎች? ምንስ ነው ስጦታቸው እና ችሎታቸው? ሰውንስ ለማገልገል የሚታመኑ ናቸው?
- የትስ ነው የሰለጠኑ አገልጋዮች አገልግሎት የሚጀምሩት? በሚመደቡበትስ አካባቢ ያለ መሰረታዊ ፍላጎት እና ቁልፍ ጉዳይ ምንድን ነው? መቼስ ነው አገልግሎታቸውን በዚህ ስፍራ የሚጀምሩት? ለማንስ ነው ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡት? ምንስ ነው የስራ ኃላፊነታቸው የሚሆነው?

**ክፍል (phase) 6፡- ማብዛት (ሐዋ 1፡8)**

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- የቤተክርስቲያን ተከላ ቡድን ይመሰርቱ ዘንድ መሪዎችን አሰልጥን
- የቤተክርስቲያን ተከላ የሚጠይቀውን የተለያየ የአገልግሎት ስፍራ መሸፈን ይችሉ ዘንድ ለእያንዳንዱ ዘርፍ መሪዎችን አሰልጥን
- ሰዎች አገልግሎት ለመጀመር የሚያስቡባቸውን አዳዲስ አካባቢዎችን አጥና
- ጥናት በተደረገበት ቦታ የወንጌል ስርጭት የሚጀመርበትን እቅድ አውጥተህ ተንቀሳቀስ
- ከእናት ጋር በዚህ አገልግሎት ሊሰማሩ የሚችሉ መሪዎችን ማቋቋም እና ማሰማራት

**ቁልፍ ጉዳይ፡-**

- ምን አይነት ጥናት ነው መደረግ ያለበት? ማንስ ነው የሚያጠናው? በአካባቢው የሚኖሩ እና በወንጌል ያልተደረሱ የማህበረሰብ ክፍሎች እሉ? ከእነርሱስ መካከል ለመሪነት ቢሰለጥኑ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አሉ?

- በዚህ ጉዳይ ተገቢ ናቸው ሳልናቸው ሰዎች ምን አይነት ግብ ሲዘጋጅ እና ሲቀርብ የሚገባው? ይህን አገልግሎት በተመለከተ የሚደረግ የጸሎት ድጋፍን ስመምራት ማን ኃላፊነቱን መውሰድ ይችላል?
- የአዳዲስ ቤተክርስቲያን ተከላን በተመለከተ የበላይ ጠባቂን ማን ሊሾም ይችላል?
- ለዚህ እንቅስቃሴ ይረዳ ዘንድ ስልጠና ለመስጠት የሚረዳ የስልጠና አገልግሎት በተለያየ የመሪነት እርከን ላይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል? ማንስ ነው ስልጠናውን የሚሰጠው? እንዴትስ ነው የስልጠናው በጀት የሚሸፈነው?

**ክፍል** (phase) 7፡- **እንቅስቃሴ** (ኢሳ 11፡9)

**ተግባራዊ እንቅስቃሴ፡-**

- በአገሬቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች ድረሱ
- እንቅስቃሴውን የምታሰፉበት መመሪያ አዘጋጁ
- ባህል ዘለል የተልዕኮ አገልጋዮችን የሚደግፉ ቡድኖችን አዘጋጁ
- የምልጃ እና የምስጋና ጸሎት ቡድኖችን አደራጁ
- ክልል አቀፍ/ አገር አቀፍ ግቦችን አስቀምጡ
- ለዚህ እንቅስቃሴ ቁልፍ አመራር መስጠት ለሚችሉ ግለሰቦች ስልጠና አዘጋጁ

**ቁልፍ ጉዳዮች፡-**

- እንቅስቃሴው ራሱን የሚያበቃ፣ ራሱን የሚደግፍ እና ራሱን በራሱ የሚመራ ነው? ካልሆነ እንዲህ ይሆን ዘንድ ምን መደረግ ይኖርበታል?
- ያልተደረሰ የሚባል ክልል ወይንም የማህበረሰብ ክፍል የቱ ነው? እነዚህን ለመድረስ ምን አይነት የተልዕኮ እቅድ እንድናዘጋጅ ነው የጌታ መንፈስ እየመራን ያለው?
- ምን አይነት ስልጠና ነው እንቅስቃሴው የሚፈልገው? እንዴትስ ሊደገፍ ይችላል?

- ለዚህ እንቅስቃሴ "የሐዋርያትን አዩነት" ምሬት ሊሰጥ የሚችለው? እንዲህ ካሉ ሠሪዎች ጋር በህብረት እንሰራለን? እንዴትስ አድርገን እንዲህ ያሉ ሠሪዎችን ማበረታታት እና መደገፍ እንችላለን?



**የጠቅላላው ቡድን ሪፖርት መቀበያ ጊዜ (30 ደቂቃ)**

**የቡድን መሪው መምሪያ፡-**

- ለእያንዳንዱ ቡድን 5 ደቂቃ በመስጠት ለጠቅላላው ተሳታፊ ስለደረሳቸው ክፍል ሊተገብሩት ያቀዱትን እንዲያቀርቡ እድል ስጣቸው።

# ክፍለ ትምህርት 5

# ትናንሽ ቡድን ለምን አስፈለገ?

### ለስትናንሽ ቡድኖች አስፈላጊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት (5 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "በዚህ ክፍለ ትምህርት ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥና ክፍሎች ለወንጌል ስርጭትና ደቀመዝሙርነት ስልጠና የቤተክርስቲያን ተከላ ማዕከላዊ አሳቦች እንደሆኑ እንማራለን፡፡ ይህን ክፍለ ትምህርት ስንማር ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን የሚለውን ቃል በመጠቀም እስከመጨረሻው እንዘልቃለን፡፡"

ትናንንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድንን ትርጉም እንዲህ አስቀምጠነዋል፤ ጥቂት የሰው ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች <u>ወንጌል ስርጭትን</u> ፣ <u>ደቀመዝሙር ማድረግን</u>፣ እና <u>አገልግሎትን</u> ዓላማቸው አድርገው በመሰባሰብ <u>የእግዚአብሔር ቃልን</u> በማጥናት <u>ጤናማ አምልኮ</u> የሚካሄድበት አዲስ ቤተክርስቲያን እንዲመሰረት ድርሻቸውን የሚወጡበት ስብስብ ነው፡፡

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ጠቅላላውን ተሳታፊ የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቅ፡-
    1. አሁን እኛ ከላይ ትርጉም እንደሰጠነው አይነት ትናንሽ የጥናት ቡድኖች በአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን ወቅት ነበር?
    2. ምንድን ነው የክርስቲያን ትናንሽ የጥናት ቡድኖችን ከሌሎች ቡድኖች የሚለየው?

**ለስትናንሽ ቡድኖች የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብን የማግኘት ተግባራዊ ልምምድ (15 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ጠቅላላውን ተሳታፊ በአራት ቡድን ክፈል

- ለእያንዳንዱ ቡድን ጥያቄ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፊል ማጣቀሻ አከፋፍል
- እያንዳንዱ ቡድን የተሰጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቦ ጥያቄዎችን እንዲመልስ መልሱንም በሪፖርት መልክ ለጠቅላላው ቡድን ለማቅረብ እንዲያዘጋጅ አበረታታ
- ሁሉም ቡድኖች በአንድ ክፍል ውስጥ ሆነው እንዲሰሩ አድርግ
- እያንዳንዱ ቡድን ጥያቄውን ለመመለስ አስር ደቂቃ መውሰድ እንዳለበት አስታውስ
- ከአስር ደቂቃ በኋላ (ሁሉንም ተሳታፊ አንድ ላይ ከመሰብሰብህ በፊት) እያንዳንዱ ቡድን እንዴት ጥያቄዎቹን እንደመለሰ በአጭሩ እንዲነግርህ አድርግ፡፡

**ቡድን 1፡- የአዲስ ኪዳን ትናንሽ ቡድኖች ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ምን አይነት ተግባር ፈጽመዋል?** (ሐዋ 4፡20፤ 5፡42፤ 20፡20)

**ቡድን 2፡- የአዲስ ኪዳን ትናንሽ ቡድኖች ሰዎችን ደቀመዝሙር በማድረጉ ረገድ ምን አይነት ተግባር ፈጽመዋል?** (ሐዋ 6፡4፤ ቆላ 4፡17)

ቡድን 3፡- የአዲስ ኪዳን ትናንሽ ቡድኖች ህብረትን በማጠንከሩ ረገድ ምን አይነት ሚና ነበራቸው? (ሐዋ 2፡42፤ ዕብ 10፡25፤ ሐዋ 20፡7፣11)

ቡድን 4፡- የአዲስ ኪዳን ትናንሽ ቡድኖች አምልኮን በማሳሰጡ ረገድ ምን አይነት ሚና ነበራቸው? (ሐዋ 1፡14፤ 2፡47፤ ቆላ 4፡2)

## ከትናንሽ ቡድኖች የሚገኝ ጥቅም

**ትናንሽ ቡድንን መተንተን** (20 **ደቂቃ**)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከዚህ ቀደም በነበሩበት ቡድን በመሆን ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ስለሩቱም ቡድን አካፍለህ አቅርብ፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን መልሱን ለሌሎች ቡድኖች ማቅረብ በሚያስችለው መልኩ መልሱን እንዲያዘጋጅ አበረታታ
- የሚቻል ከሆነ እያንዳንዱ ቡድን መልሱን በትልቅ ወረቀት ላይ በማስፈር ክፍል ውስጥ ሊሰጠፍ በሚችል መልኩ እንዲጽፍ አበረታታ፤ ከዚያም መማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ለጥፈው፡፡

**ቡድን 1፡- ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ለወንጌል ስርጭት ምን አይነት አስተዋጽዖ ያበረክታሉ?**

በትናንሽ ቡድኖች ሊከወን የሚችልና ወንጌልን ለማድረስ የሚጠቅም ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ምን ምን ናቸው?

**ቡድን 2፡- ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች አማኞችን ደቀመዝሙር ለማድረግ ምን አይነት አስተዋጽዖ ያበረክታሉ?**

ትናንሽ ቡድኖች የሚከውኑት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በእገዛ፣ ያለንን ማካፈልና ማማከርና ድጋፍ ላይ ምን አይነት ለውጥ ያመጣል?

**ቡድን 3፡- ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ህብረትን ለማጠንከር ምን አይነት አስተዋጽዖ ያበረክታሉ?**

በትናንሽ ቡድኖች የሚከወን እና አንዱ ሌላው ያበረታ ዘንድ ሚረዳ፣ ያለንን ማካፈል እና በክርስትስ ውስጥ ያለን ህብረት የሚያጠነክር ምን አይነት ተግባር አለ?

**ቡድን 4፡- ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ለአምልኮ ምን አይነት አስተዋጽዖ ያበረክታሉ?**

በትናንሽ ቡድኖች የሚከወን እና ለእግዚአብሔር ምስጋና እና ክብር የሚሆን ምን አይነት ተግባር እናገኛለን?

**በጠቅላላ ተሳታፊዎች የሚደረግ ሪፖርት እና ውይይት**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- እያንዳንዱ ቡድን ለተሰጠው ጥያቄ የሰጠውን መልስ ለጠቅላላ ቡድኑ እንዲያብራራ እድል ስጥ (10 ደቂቃ)
- ይህንን ክፍለ ትምህርት ለመጠቅለል ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩበት

1. መሪዎችን በማብቃቱ ረገድ ትናንሽ ቡድኖች የሚሰጡት ጥቅም ምንድን ነው?

2. በዚህ ክፍለ ትምህርት ያጠናነውን ሁሉ በማጤን ትናንሽ ቡድኖች ለቤተክርስቲያን ተከላ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

# ክፍል ትምህርት 6

# መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስተምረን መፍቀድ (60 ደቂቃ)

## መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት እና እውነትን ከመጽሐፉ መልዕክት መውሰድ፤ ክፍል 1

**መልእክት ከመጽሐፉ መውሰድ ከመልዕክትን በመጽሐፉ መደገፍ ጋር ሲወዳደር (2ጢሞ2፡15) (10 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች ያለውን ማውጫ ዝርዝር በመጠቀም መልዕክትን ከመጽሐፉ በመውሰድ እና መልዕክትን በመጽሐፉ በማስደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ፡፡

1. መልዕክትን በመጽፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስደገፍ የአጠናን ዘዴ

I. መልእክትን በመጽሐፍ ቅዱስ የማስደገፍ የጥናት ዘዴ አመክንዮ

ይህን ጥናት ስንጀምር ቀድሞ ባወቅነው እና በተቀበልነው አሳብ ላይ ተንተርሰን ድምዳሜ ላይ ለመድረስ "የምንወርድበት" መንገድ ነው፡፡

II. መልዕክትን በመጽሐፉ የማስደገፍ የጥናት ዘዴ

አስተማሪው እርሾ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአትን ወክሎ ደጋግሞ መቅረቡን አንደ ወካይ ህግ አድርጎ ያቀርባል እናም በማቴ 13፡33 ላያ ያለው እርሾ የሚለው ቃል ኃጢአትን ወክሎ እንደቀረበ አንገምታለን፤ እስኪ ክፍሉን እናንብብ፤ በዚህ ክፍል ኃጢአትን ወክሎ ያቀረበ ይመስላችኋል?

III. መልዕክትን በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ማስደገፍ የጥናት ዘዴ

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች በአብዛኛው ሲያስተምሩ የሚፈልጉትን ያውቃሉ፤ ማስተማር ሲፈልጉ የሚያደርጉት አንድ ነገር የእነርሱን አሳብ ይደግፋል ብለው ያመኑበትን ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መፈለግ ነው፡፡ ለምንድን ነው እንዲህ ያለው

የጥናት ዘዴ የክፍሉን እውነተኛ መልዕክት በተዛባ ሁኔታ የመረዳት ችግር የሚፈጥረው?

2. ከመጽሐፉ መልዕክትን የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ



I. መልዕክትን ከመጽሐፉ መውሰድ አመክንዮ

የቀረበውን እውነታ ለመረዳት ከመነጨ ፍላጎት የምንባቡን ሐሳብ ምንነት <u>መፈተን</u>

II. ከመጽሐፉ መልዕክትን የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

የማቴዎስ 13፡33ን <u>ምንባብ</u> እና <u>አውድ</u> በጥንቃቄ በማጥናት "እርሾ" የሚለው ቃል ምንን ወክሎ እንደገባ ይመረምሩ፡፡

III. መልዕክትን ከመጽሐፉ መውሰድ የተሻለ የጥናት ዘዴ ነው

ሰዎች መጽሐፉን በማጥናት ሂደት እውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ ከተፈለገ ይህ የጥናት ዘዴ ወሳኝ መንገድ ነው፡፡

**ከመጽሐፉ መልእክትን የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ደረጃዎች (20 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡- በምታስተምርበት ወቅት ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ስፍራ እየሞሉ እንዲከታተሉ አሳስባቸው፡፡**

1. <u>ምልከታ</u>- ምን ይላል?

2. <u>መተርጎም</u>- ምን ማለት ነው?

3. <u>ማዛመድ</u>- ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል?

**ከመጽሐፉ መልዕክትን የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጉርሻ**

ጠንካራ መሰረት ላይ ይመሰርተናል፤ ይህ መሰረትን መጣል የሚጀምረው ጥልቅ በሆነ ምልከታ ነው፡፡ የምታጠኑትን መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እውነተኛ መልዕክት ለማወቅ በጥንቃቄ የክፍሉን ሀሳብ መመርመር እና ማወቅ ተቀባይነት ያለው የማዛመድ ብቃት ለማግኘት ይረዳል፡፡

**ክፍሉን ለማጥናት በቂ ጊዜ ውሰድ፤** የክፍሉ ሀሳብ ምን እንደሆነ ለማወቅ ግልብ የሆነ ንባብ በማድረግ ድምዳሜ ላይ አትድረስ፡፡ በፍጹም ብዥታን የሚፈጥር እና ጥያቄ የሚያስነሳ የማዛመድ ሀሳብ አታምጣ፡፡

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- እዚህ ላይ ተሳታፊዎች ከመጽሐፉ ሀሳብ በመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ በተመለከተ ጥያቄአቸውን እንዲያቀርቡ አበረታታ፡፡ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ በቂ ጊዜ ውሰድ፡፡

### ከመጽሐፉ ሀሳብ በመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ሞዴል ጥናት (25 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ዮሐ 1፡1-5 በዚህ የአጠናን ዘዴ መሰረት ያጥኑ፡፡ ታዲያ ጥናቱ በሚደረግበት ወቅት ተሳታፊዎችን ማበረታታት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጥናቱ እየተካሄደ ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ክፍት ቦታ እንዲሞሉ አበረታታቸው፡፡

## ዮሐንስ 1፡1-5

## ከመጽሐፉ ሀሳብ የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

1. ምልከታ፡- የመጽሐፉ ምንባብ ምን ይላል?

2. መተርጎም፦ የመጽሐፉ ክፍል አሳብ ትርጉም ምንድን ነው?

3. ማዛመድ፦ ምን እናድርግ/ምን አናድርግ?

## ለሞጁል 2 የሚሆን የትግበራ እቅድ፦ በግል የሚደረግ ከመጽሐፉ አሳብ የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ (5 ደቂቃ)

ቀጣዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል በዚህ የአጠናን ዘዴ ተጠቅመን ምልከታን ለማከናወን ከአንድ አንቀጽ ያልበለጠ ክፍል ውሰዱ። ለመረጣችሁት አንድ አንቀጽ በትንሹ አንድ ሰአት ወስዳችሁ በመንፈሳችሁ እግዚአብሔር የውስጥ አይናችሁ እንዲበራ እና በዚህ ክፍል የተገለጠውን እውነት ማወቅ ትችሉ ዘንድ እየጸለያችሁ ምልከታችሁን አካሂዱ። ከዚያ ምልከታችሁን በጽሑፍ አስፍሩ። ምን ተማራችሁ? ከዚህ ክፍል የተማራችሁትን በቀጣይ ክፍለ ትምህርት አብረዋችሁ ለሚሰለጥኑ ተሳታፊዎች ለማቅረብ ተዘጋጁ።

# ቀጣዩ ምንድን ነው?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ፈቃደኛ የሆኑትን መርጠህ በእነርሱ አመለካከት መልስ ይሆናል ብለው ያሰቡትን በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታቸው፡-
  1. ጤናማ ቤተክርስቲያን ምንድን ነው?
  2. ጤናማ ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚጠቅም መሰረታዊ ሂደት ምንድን ነው?
  3. ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል ለምን ያስፈልጋል?
- ተሳታፊዎችን እንደ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች በዚህ ስልጠና ያስደመማቸው፣ ያበረታታቸው ወይንም ያነቃቃቸው በዚህ ስልጠና የተማሩት እውነት ካለ እንዲናገሩ እድል ስጣቸው፡፡
- ሁለቱን የትግበራ እቅዶች እንደገና ቀኝት አድርግ (ክፍለትምህርት 3 እና 6)፤ ከእነዚህ ጋር የተገናኙ ማንኛውንም ጥያቄዎች መልስ፡፡
- በአንድነት ሆናችሁ በመዘመር እና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮችን በመባረክ በጸሎት ስልጠናውን አጠናቁ፡፡

ወደሚቀጥለው ሞጁል ከመሻገራችሁ በፊት የሚከተሉትን ታደርጉ ዘንድ እንመክራለን፡-

- ➢ አስር ሰዎችን ተዋወቅ
- ➢ ለአምስት ሰው የክርስቶስን ወንጌል ተናገር
- ➢ አንድ አነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን መስርት

ለሞጁል 2 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡- የመከታተያ ቅጽ

- ➢ ስለ"መጨረሻ" እቅድ የተሰጠውን የቤትስራ አጠናቅ (ክፍለ ትምህርት 3)
- ➢ ከመጽሐፉ አሳብ የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን ተጠቀማችሁ ማጥናትን ተለማመዱ (ክፍለ ትምህርት 6)